መመሪያ ቁጥር 998/2016

# የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራም ቅጂ አያያዝ
# መመሪያ ቁጥር 998/2016

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን

መጋቢት፣ 2016 ዓ.ም
<u>አዲስ አበባ</u>

# *መመሪያ ቁጥር 998/2016*
# *<u>የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራም ቅጂ አያያዝ መመሪያ</u>*

በብሮድካስት አገልግሎት የተሰራጨ ፕሮግራም ለማስረጃነት በተፈለገ ጊዜ ማግኘት እንዲቻል ተቀርፆና ደህንነቱ ተጠብቆ መቀመጥ ያለበት መሆኑ በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀፅ 66 በመደንገጉ፤

በብሮድካስት አገልግሎት የተሰራጨ እና ተቀርጾ የተቀመጠ የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራም በአግባቡ ተደራጅቶ እንዲያዝ ለማድረግ፤

በብሮድካስት አገልግሎት ከተሰራጨ ፕሮግራም ጋር በተያያዘ ቁጥጥር ለማድረግ ወይም የቀረበ ቅሬታን ወይም ጥቆማን ለመመርመር ፕሮግራሙ ተቀርጾ እና ደህንነቱ ተጠብቆ እንዲቆይ አሰራር መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀጽ 12(7) እና አንቀፅ 90(2) መሠረት ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ቦርድ ወጥቷል፡፡

## *<u>ክፍል አንድ</u>*
## *<u>ጠቅላላ</u>*

### *1. <u>አጭር ርዕስ</u>*

ይህ መመሪያ *"የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራም ቅጂ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 998/2016"* ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### *2. <u>ትርጓሜ</u>*

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ ***"የብሮድካስት አገልግሎት"*** ማለት ከምድር ወደ አየር አስተላላፊ፣ በሬዲዮ ሞገድ፣ በኬብል፣ በሳተላይት፣ ወይም እነዚህን በማቀናጀት ሥራ ላይ በሚውሉ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ወይም የሬዲዮና የቴሌቪዥን ማሰራጫዎች ወይም በኢንተርኔት አማካይነት ሕዝብን ለማሳወቅ፣ ለማስተማር ወይም ለማዝናናት በድምጽ ወይም በምስል ወይም በድምጽና በምስል በክፍያ ወይም ያለክፍያ የሚተላለፍ ወይም

የሚሰራጭ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ፕሮግራም ስርጭት አገልግሎት ነው፡፡

2/ ***"ባለፈቃድ"*** ማለት በመገናኛ ብዙሃን አዋጁና በአዋጁ መሰረት በሚወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች መሰረት የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሲሆን፣ የመገናኛ ብዙሃን አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በህጋዊ መንገድ የብሮድካስት አገልግሎት በመስጠት ላይ ያለ ሰውንም ይጨምራል፡፡

3/ ***"ፕሮግራም"*** ማለት በድምፅ፣ በምስል ወይም በድምፅና በምስል ተቀነባብሮ ሕዝብን ለማሳወቅ ወይም ለማስተማር ወይም ለማዝናናት ወይም ሁሉንም አካቶ በብሮድካስት አገልግሎት አማካኝነት የሚቀርብ ዝግጅት ነው፤

4/ ***"ዜና"*** ማለት አካባቢያዊ፣ ክልላዊ፣ ሀገራዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸው እና ወቅታዊ የሆኑ ጉዳዮችን በሚመለከት በብሮድካስት አገልግሎት አማካኝነት የሚቀርብ የዘገባ ሥርጭት ነው፤

5/ ***"ማስታወቂያ"*** ማለት ምርት፣ አገልግሎት፣ ስም፣ አርማ፣ ምልክት፣ አላማ ወይም ሌላ ተዛማጅ መልዕክት እንዲተዋወቅ ወይም እንዲሸጥ የሚተላለፍ መልዕክት ነው፤

6/ ***"ቦርድ"*** ማለት የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ቦርድ ነው፤

7/ ***"ባለሥልጣን"*** ማለት የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ነው፤

8/ ***"ሰው"*** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

## 3. *<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>*

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመ የሕዝብ፣ ልዩ የሕዝብ፣ የንግድ የማኅበረሰብ እና የሃይማኖት ብሮድካስት አገልግሎት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት
# ስለ ብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራም ቅጂ አያያዝ

## 4. ፕሮግራም ቀርፆ ስለመያዝ

ማንኛውም ባለፈቃድ፡-

1/ ያሰራጨውን ፕሮግራም ቀርፆ ቢያንስ ለ30 ቀናት ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

2/ በፕሮግራሙ ውስጥ ቀደም ሲል የተቀረፀን ፕሮግራም ወይም ፊልም አካቶ ያሰራጨ ከሆነም አብሮ ቀርፆ ቢያንስ ለ30 ቀናት ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

3/ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከተው የጊዜ ገደብ ቢኖርም፡-

ሀ) በተላለፈው ፕሮግራም ላይ ቅሬታ ከቀረበ ወይም ለፍርድ ቤት የክስ ሂደት፣ ሙግት፣ ቅሬታ ወይም ሌላ ማንኛውም ዓይነት ክርክር መነሻ ከሆነ እነዚህ ጉዳዮች አግባብ ባለው ህግ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚያገኝ ጊዜ ድረስ የፕሮግራሙ ቅጂ በአግባቡ ተይዞ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 5. ተቀርፆ ስለሚያዘው ፕሮግራም ትክክለኛነት

ተቀርጾ የተቀመጠ የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራም ማናቸውም አይነት መለዋወጥ ያልተደረገበት የተሰራጨው ፕሮግራም ትክክለኛ ቅጂ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 6. ፕሮግራሙ ተቀርፆ ስለሚያዝበት መሳሪያ

ባለፈቃዱ በብሮድካስት አገልግሎት ያሰራጨውን ፕሮግራም ጥራት ባለው፣ ጊዜው በሚጠይቀው እና ደረጃውን በጠበቀ የመረጃ ቋት አማራጭ መሳሪያዎችን ተጠቅሞ ቀርፆ መያዝ እና ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 7. የተቀረፀው ፕሮግራም ስለሚያዝበት ሁኔታ እና ቦታ

1/ ተቀርጾ የተቀመጠ የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራም ቅጂ ደህንነቱ ተጠብቆ እንዲቆይ ሊደረግ ይገባል፡፡

2/ ተቀርጾ የተቀመጠ የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራም ቅጂ፡-

ሀ) በተፈለገ ጊዜ በቀላሉ ሊገኝ በሚችልበት ሁኔታ ተመዝግቦ እና ተደራጅቶ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

ለ) የብሮድካስት ጣቢያው በሚገኝበት ተለይቶ በሚታወቅ ቦታ መቀመጥ አለበት፡፡

3/ ባለፈቃዱ ተቀርጾ የተቀመጠ የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራም ቅጂ፡-

ሀ) የሚቀመጥበትን ቦታ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ እና

ለ) በማናቸውም የሥራ ሰዓት በጣቢያው መገኘቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

4/ የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራም ተቀርጾ የተቀመጠበት ማናቸውም መሳሪያ ከሚከተሉት መረጃዎች ጋር ተደራጅቶ መቀመጥ ይኖርበታል፡-

ሀ) የብሮድካስት አገልግሎት ጣቢያውን ስም

ለ) የፕሮግራሙን ስም፣

ሐ) የፕሮግራሙ የቆይታ ሰዓት፣

መ) ፕሮግራሙ የተሰራጨበትን ቀን፣ ሰዓት እና ዓመት ምህረት፣

ሠ) በፕሮግራሙ ውስጥ ቀደም ሲል የተሰራጨ ፕሮግራም ተካትቶ ከሆነም መካተቱን፣

ረ) የፕሮግራሙን አዘጋጅ ስም እንዲሁም ሌላ አስፈላጊ መረጃ፡፡

## 8. *ከፕሮግራሙ ጋር ተያያዥ የሆኑ ተጨማሪ ሰነዶችን ስለመያዝ*

ማንኛውም ባለፈቃድ በብሮድካስት አገልግሎት ካሰራጨው ፕሮግራም ጋር በተያያዘ ለማሰረጃነት የተጠቀመበትን ሰነድ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀጽ (4) በተመለከተው መሰረት ከተሰራጨው ፕሮግራም ጋር በማገናዘብ ይዞ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 9. *ተቀርፆ ስለተያዘ የፕሮግራም ቅጂ አጠቃቀም*

1/ ተቀርጾ የተቀመጠ የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራም እንደገና ጥቅም ላይ ሲውል፡-

ሀ) ከሌላ ፕሮግራም የተለየ መሆኑ በግልጽ እንዲታወቅ ሆኖ መዘጋጀትና መሰራጨት፣ እንዲሁም

ለ) ከፋይል የተገኘ መሆኑ እና ቀደም ሲል የተሰራጨበት ቀን እና ዓመት ምሕረት መግለጽ ይኖርበታል፡፡

2/ ተቀርጾ የተቀመጠ የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራም እንደገና ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ፡-

ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) መሰረት ተቀርፆ ቢያንስ ለ30 ቀናት መቀመጥ፣ እና

ለ) ቀደም ሲል የተሰራጨው ፕሮግራም በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ (4) ከተዘረዘሩት መረጃዎች ጋር ተደራጅቶ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 10. ተቀርፆ የተያዘውን ፕሮግራም ስለማቅረብ

1/ ባለፈቃዱ ለሚመለከተው አካል የቀረበ ጥቆማን ወይም ቅሬታን ለመመርመር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ጥያቄ ሲቀርብለት ቀርጾ ያስቀመጠውን ፕሮግራም ትክክለኛ ቅጂ በራሱ ወጪ ለባለሥልጣኑ ወይም በሕግ መሰረት ጉዳዩን ለሚመለከተው አካል ወዲያውኑ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት ተቀርፆ የተቀመጠ የፕሮግራም ቅጂን ከባለፈቃዱ የተረከበ ሰው ከክትትል እና ቁጥጥር ሥራ ውጪ ለሌላ ሕገ ወጥ አላማ ማዋል የለበትም፡፡

3/ በሌላ ሕግ የተደነገገው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለፈቃዱ ቀርፆ ያስቀመጠውን የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራም ቅጂ ማግኘት ለሚፈልግ ሰው ለመስጠት ይችላል፡፡

## 11. ቁጥጥር ስለማድረግ

1/ ባለሥልጣኑ በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ እና በዚህ መመሪያ መሰረት ቁጥጥር ለማድረግ እና የሚሰጠው ውሳኔ መከበሩን ለማረጋገጥ የሚመድበው ኢንስፔክተር የብሮድካስት አገልግሎት በሚያካሂድ ድርጅት ውስጥ በሥራ

ሰዓት ለመግባት እና ተቀርጾ የተያዘ ፕሮግራም ቅጂን፣ የብሮድካስት መሳሪያን እና አግባብነት ያለውን ሰነድ ለማየት እና ቅጂው እንዲሰጠው ለመጠየቅ ይችላል፡፡

2/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀፅ መሰረት ከባለፈቃዱ የተረከበውን የፕሮግራም ቅጂ፣ የሰነድ ማስረጃ እና የተፃፃፋቸውን ደብዳቤዎች የባለፈቃዱን መብት ባስጠበቀ ሁኔታ ያስቀምጣል፡፡

## 12. *የተሻረ መመሪያ እና ስለመመሪያው ተፈጻሚነት*

1/ የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራም ቅጂ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 2/2003ዓ.ም. በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

2/ ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ትእዛዝ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 13. *መመሪያውን ስለማሻሻል*

የባለሥልጣኑ ቦርድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## 14. *መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ*

ይህ መመሪያ በባለስልጣኑ ቦርድ ከጸደቀና በባለስልጣኑ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

***የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን ቦርድ***